Family Assessment Response (የቤተሰብ ግምገማ ምላሽ) ልምንድን ነው ወደ እኔ እየመጣ ያለው?

- Department of Children, Youth, and Families (የህጻናት፣ ወጣቶች፣ እና የቤተሰቦች መምርያ, DCYF) ስለ ልጅዎ ደህንነት የያዘውን ሪፖርት አግኝቷል።
- ሪፖርቱ በ Washington ግዛት የልጆች ጥቃት እና ቸልተኝነት ሕጋዊ የሆነውስ አተረጓጎም አሟልቷል (RCW 26.44.020)።
- ሪፖርቱ ልጅዎ አስቸኳይ ስጋት ላይ እንደ ነበረ አልተናገረም።
- DCYF የልጅዎን ደህንነት ለመጠበቅ ከእርስዎ ጋር መስራት ይፈልጋል።

ስለ ጉዳዬ ስጋቶች ቢኖሩኝ ማንን ነው የማናግረው?

ጉዳይዎ እንዴት እንደሚስተናገድ ቅሬታ ወይም ስጋት ካለዎት፣ የFAR ጉዳይ ሰራተኛ ተቆጣጣሪዎ ጋር ይደውሉ።

ስጋቶችዎ አሁንም ካልተቀረፉ የአካባቢው አስተዳደር ጋር መደወል ይችላሉ።

እርዳታ ለማግኘት በማንኛውም ሰዓት ለምርጫ ግንኙነት ቢሮ(Office of Constituent Relations) በ1-800-723-4831 መደወል ይችላሉ።

-ወይም-

ለቤተሰብ እና የልጆች እንባ ጠባቂ ቢሮ (Office of the Family & Children's Ombuds)* በ 1-800-571-7321 በኩል መደወል ይችላሉ።

*ይህ ወኪል ከ *DCYF* የተለየ ነው። ስለ *DCYF* ያሉትን ስጋቶች የመረምራል።

የዚህን ሰነድ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ ፣ እባክዎን *DCYF Constituent Relations (የ DCYF አባል ግንኙነቶች)* ን በ*(1-800-723-4831 | 360-902-8060 ፣ **ConstRelations@dcyf.wa.gov**)* ያነጋግሩ።

የDCYF ዕትም CWP_0023 | DSHS 22-1534 AM (07-2021) Amharic

Family Assessment Response (የቤተሰብ ግምገማ ምላሽ, FAR)

ቤተሰቦችን ለማጠናከር እና ለመደገፍ ያለው የ*CPS* መንገድ

Washington State Department of CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

Family Assessment Response (የቤተሰብ ግምገማ ምላሽ, FAR) ምንድነው?

ለአንዳንድ የልጆች ጥቃት እና ቸልተኝነት ሪፖርቶች ምላሽ ለመስጠት ፣ FAR ለ Washington State Child Protective Services (ዋሽንግተን ግዛት የልጆች ጥበቃ አገልግሎቶች) የተለየ መንገድ ነው። ከ FAR በፊት ፣ CPS በልጆች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት እና ቸልተኝነት ላይ የወጡ ሪፖርቶች ላይ በምርመራ ምላሽ ሰጥቷል።

FAR ከቤተሰቦች ጋርም ይሰራል፦

- ለህጻናት ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ተጠያቂ ወላጆች ሳያገኙ በችግር ውስጥ ሲሆኑ ይረዳቸዋል።
- ከማህበረሰቦቻቸው ጋር በማገናኘት ያግዛቸዋል።

ሁለቱም መርማሪዎች እና የFAR ጉዳይ ሰራተኞች፦

- የህጻናትን ደህንነት ለመጠበቅ ከቤተሰቦች ጋር ይሰራሉ።
- የቤተሰቦችን ፍላጎቶች ይለያል።
- በወላጆች እና በማህበረሰብ ጥንካሬዎች እና ሀብቶች ላይ ይመሰረታል።
- በልጆች ፍላጎቶች ላይ ለማተኮር አስቸጋሪ የሆኑ አስጨናቂ ሁኔታዎችን ለማቃለል የሚሆኑ አገልግሎቶችን ያገኛል።

ምርመራዎች፦

- በልጁ ላይ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት መድረሱን ይወስናሉ።
- በልጆች ላይ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ተከስቷል ተብሎ የተጠረጠረ ጥቃት ወይም ቸል ባይነት ተጠያቂው ማን እንደሆነ ይለያሉ። ይህም በDCYF መዝገባት ውስጥ ተቀምጧል እና ወደፊት ከልጆች ወይም ከአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች ጋር ያለውን ሥራ ሊጎዳ ይችላል።

Family Assessment Response (የቤተሰብ ግምገማ ምላሽ) እንዴት ነው የሚሰራው?

DCYF ስለ ቤተሰብዎ ሪፖርት ሲደርሰው ፣ የFAR ጉዳይ ሰራተኛ ስለልጆችዎ ደህንነት ያለውን ነገር ለመነጋገር ከእርስዎ ጋር ይገናኛል።



የወደፊት የልጅ ጥቃትን እና ቸልተኝነትን አደጋ ለመቀነስ አገልግሎቶች ወይም ድጋፎች እንደሚያስፈልጉ ለመወሰን ፣ የጉዳይ ሰራተኛው ከእርስዎ ጋር በቅርበት ይሰራል ። የጉዳይዎ ሰራተኛ ቤተሰብዎ በችግር ውስጥ አልፈው እንዲሰሩ ያግዛቸዋል።

አብዛኛው የ FAR ጉዳዮች በ 45 ቀናት ውስጥ ይዘጋሉ። ሆኖም ግን፣ የጀመራችሁትን መልካም ሥራ የሚደግፉ አገልግሎቶችን መቀጠል ጠቃሚ ከሆነ ፣ እርስዎ እና የFAR ጉዳይ ሰራተኛ ጉዳይዎን ለ120 ቀናት ክፍትእንዲሆን ለማድረግ መምረጥ ይችላሉ።

ምርጫዎች አልዎት፦

- ከ FAR ጋር መሳተፍን መምረጥ ይችላሉ
  -ወይም-
- ባህላዊዉን የ CPS ምርመራ ስልት መጠቀምን መምረጥ ይችላሉ

ቤተሰብዎ ስለሚፈልጋቸው አገልግሎቶች ከ FAR የጉዳይ ሰራተኛዎ ጋር ካልተስማሙ፣ ስለሉ ሌሎች አማራጮች ለመነጋገር ከ FAR ሰራተኞች ጋር ስብሰባ እንዲኖራቹ መጠየቅ ይችላሉ።

የጉዳይዎ ሰራተኛ ቤተሰብዎ በችግር ውስጥ አልፈው እንዲሰሩ ያግዛቸዋል።

Family Assessment Response (የቤተሰብ ግምገማ ምላሽ) እንዴት እኔን ሊረዳኝ ይችላል?

እርስዎ እና ቤተሰብዎ ምን እንደሚፈልጉ ያውቃሉ። የFAR ጉዳይ ሰራተኛዎ ከእርስዎ ጋር በቅርበት ይሰራል፦

- በቤትዎ ውስጥ የልጅዎን ደህንነት እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ ለመለየት።
- የቤተሰብዎን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት።
- በሁሉም እድሜ እና ደረጃዎች ፣ ልጆቻችሁን ወላጅ እንድትሆኑ ለመርዳት ችሎታዎችን ለመጨመር
- ከማህበረሰብዎ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር።
- የማህበረሰብ ሀብቶችን እና አማካሪዎችን ያግኙ እንደ መኖሪያ ቤት፣ ስራ ወይም ሌሎች ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ጭንቀት የሚፈጥሩ ችግሮችን ለመፍታት።

የልጆችዎን ደህንነት ለመጠበቅ ፣ በራስ መተማመንዎን እና ችሎታዎን ለመገንባት በጋራ እንሰራለን።